PRESS RELEASE

PR24/444

# ለኢትዮጵያ በተሰጠው የተራዘመው ብድር አቅርቦት የሁለተኛ ግምገማ አይኤምኤፍ በባለሞያዎች/ስታፍ ደረጃ ስምምነት ላይ ደርሷል

**በቶሎ የሚለቀቅ**

- የአይኤምኤፍ ባለሞያዎች እና የኢትዮጵያ ባለስልጣናት የ4 አመት የዩኤስ ዶላር 3.4 ቢሊየን የሁለተኛውን ግምገማ በማድረግ በኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎች ላይ በባለሞያዎች ደረጃ ስምምነት ላይ ደርሰዋል። በአይኤምኤፍ ስራ አስፈጻሚ ቦርድ ይፋዊ ግምገማው ሲጠናቀቅ ኢትዮጵያ ዩኤስ ዶላር 251 ሚሊየን አካባቢ የሚደርስ ፋይናንስ ለማግኘት ያስችላታል።
- በገበያ የሚወሰን የውጭ ምንዛሪ ምጣኔን የሚያጠቃልለው የኢትዮጵያ አገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም ትግበራ በጥሩ ሁኔታ ቀጥሏል። የውጭ ምንዛሪ እጥረት በከፍተኛ ሁኔታ ተቃሏል፣ እና በህጋዊው እና በትይዩ ገበያው መካከልም ያለው ልዩነት ከ10 በመቶ በታች ቀንሷል።

**ዋሽንግተን ዲሲ - ህዳር 18 ቀን 2017 ዓ.ም፡-** በሚስተር አልቫሮ ፒሪስ የሚመራው የዐለም አቀፍ የገንዘብ ድርጀት የባለሞያዎች ቡድን አዲስ አበባን ከህዳር 03 እስከ 17 2017 ዓ.ም የጎበኘ ሲሆን፣ የጉብኝቱም አላማ በማሻሻያው ላይ ያሉትን እርምጃዎች ላይ እና በአይኤምኤፍ የሚደገፈውን የኢትዮጵያን የኢኮኖሚ ማሻሻያ መርሀ ግብር 2ኛ ግምገማ አውድ የአይኤምኤፍን የተራዘመ የብድር አቅርቦት ላይ ባለስልጣናት ያላቸውን የፖሊሲ የትኩረት መስኮች ላይ ለመወያየት ነው። እቅዱ ለመነሻ ጠቅላላ የገንዘብ መጠን ኤስዲአር 2.556 ቢሊየን (በጊዜው ወደ ዩኤስ ዶላር 3.4 ቢሊየን አካባቢ) በአይኤምኤፍ ስራ አስፈጻሚ ቦርድ ሐምሌ 22 ቀን 2016 ዓ.ም ጸድቆ ነበር።

በተልእኮ ማጠቃለያ ላይ ሚስተር ፒሪስ የሚከተለውን መግለጫ ሰጥተዋል፡-

"የአይኤምኤፍ የባለሞያዎች ቡድን እና የኢትዮጵያ ባለስልጣናት በተሰጠው የብድር አቅርቦት መርሃ ግብር ላይ በኢትዮጵያ የኢኮኖሚ መርሀ ግብር 2ኛው ግምገማ ላይ በባለሞያ ደረጃ ስምምነት ላይ ደርሰዋል። ስምምነቱ በአይኤምኤፍ ስራ አመራር እና ስራ አስፈጻሚ ቦርድ በሚቀጥሉት ሳምንታት በሚደረገው ማጽደቅ የሚጠብቅ ይሆናል። የስራ አስፈጻሚ ቦርዱ ግምገማ ሲጠናቀቅ ኢትዮጵያ ጠቅላላ የገንዘብ መጠን ኤስዲአር 191.70 ቢሊየን (በጊዜው ወደ ዩኤስ ዶላር 251 ሚሊየን አካባቢ) የምታገኝ ይሆናል። የወደፊት ግምገማዎች በየ6 ወር የጊዜ ሰሌዳ ይሆናል።

"በገበያ የሚወሰን የውጭ ምንዛሪ ምጣኔ የሚያጠቃልለው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ማሻሻያ መርሃ ግብር ትግበራ በጥሩ ሁኔታ ቀጥሏል። የውጭ ምንዛሪን የማስተላለፍ መስፈርቶች መቀነስ፤

700 19th Street NW
Washington, DC 20431
USA

በውጭ ምንዛሪ በባንኮች መካከል ያለውን እንቅስቃሴ መጨመረ እና በአገር ውስጥ በባንኮች መካከል ያለውን የገንዘብ ግብይት በተሳካ ሁኔታ ማስጀመር በቅርቡ የተጀመረዉን ጥሩ አካሄድ አግዘዉታል። የውጭ ምንዛሪ እጥረት በከፍኛ ሁኔታ ቀንሷል፣ እና በጥቅምት ወር በትንሹ ከጨመረ በኋላ በህጋዊው እና በትይዩ ገበያው መካከልም ያለው ልዩነት ከ10 በመቶ በታች ቀንሷል።

“ጥንቃቄ በተሞላበት ፖሊሲ የሚደገፈው የማክሮ ኢኮኖሚ መረጋጋት እና እስካሁን የውጭ ምንዛሪ ማሻሻያው የዋጋ ግሽበት ላይ ያለው ውስን ተጽኖ፣ ወደፊት የሚኖሩት የኢኮኖሚ እድገት ሁኔታዎች ተስፋ ሰጪ እንዲሆን አድርጎታል። በሚኒስትሮች ምክር ቤት በቅርቡ የጸደቀው የተጨማሪ በጀት ትግበራ በፕሮግራሙ አላማዎች መሰረት የፊሲካል ግቦችን በማስጠበቅ የገንዘብ ፍስት ውስነቶችን (ሊኩዊዲቲ እጥረተን) ለማቃለል የሚረዱ ይሆናሉ። በመካከለኛ ጊዜ ውስጥ ዝቅተኛ እና የተረጋጋ የዋጋ ግሽበትን ሂደትን ለማረጋገጥ፣ በወለድ ምጣኔ መሰረት ወደ ሚያድርገው የገንዘብ ፖሊስ ሽግግር ወቅት ጥብቅ የገንዘብ እና የፋይናንስ ሆኔታዎች ማስቀጠል ጠቃሚ ይሆናል።

“የባለሞያዎች ቡድኑ ለነበሩት ጥሩ ውይይቶች እና በአይኤምኤፍ የሚደገፈውን የኢኮኖሚ መርሃ ግብር ስኬት በማረጋገጡ ላይ ላላቸው ጠንካራ እርምጃ ለባለስልጣናቱ ምስጋንውን ያቀርባል። ቡድኑ ከገንዘብ ሚኒስቴሩ ሚኒስትር አህመድ ሺዴ፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዢ ከሆኑት ማሞ ምህረቱ፣ የገንዘብ ሚኒስትር ድኤታ ከሆኑት እዮብ ተካልኝ እና ሌሎች ከፍተኛ ባለስልጣናት ጋር ተገናኝቷል። ባለሞያዎቹ በተጨማሪም በብዙ ዘርፎች ከሚንቀሳቀሱ ባንኮች እና የንግድ ተቋማት ጋር ውጤታማ ውይይቶች ነበሩት።

700 19th Street NW
Washington, DC 20431
USA